የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

(ሰኔ 17- 24/2016 ዓ.ም)
June 17- July 1/2024

## በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

### 1. _የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ለመሆን ከአዲስ አበባና ከኦሮሚያ የተወከሉ ዕጩዎች ቀረቡ

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. እንደሚካሄድ፣ ለሚጠበቀው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምርጫ የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ ለመያዝ የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን በአሁኑ ወቅት እየመሩ የሚገኙ ፕሬዚዳንቶች በዕጩነት መቅረባቸው ታወቀ፡፡

**Reporter** ***June 26, 2024***

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምርጫውን ለማካሄድ አባል ምክር ቤቶች ዕጩዎችን እንዲያሳውቁ ባቀረበው ጥሪ መሠረት እስካሁን ለፕሬዚዳንትነት እንዲወዳደሩ በየምክር ቤቶቻቸው ቦርድ ተመርጠው በዕጩነት ከቀረቡት መካከል፣ የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራና የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ቀዳሚ ሆነዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/130879/

### 2. _አምራች ኢንዱስትሪዎች በቀናት ውስጥ የቦታና የቤት ግብር ካልከፈሉ ይታሸጋሉ መባሉ ቅሬታ አስነሳ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አዲስ ያወጣው የቦታና የቤት ግብር ተመን እንዲያስተካክልላቸው ጥያቄ ያቀረቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምላሽ ሳያገኙ ግብሩን በቀናት ውስጥ ካልከፈሉ ድርጅቶቻቸው እንደሚታሸጉ የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው መደረጉ እንዳሳሰባቸው ተገለጸ፡፡

**Reporter** ***June 30, 2024***

ከኢትዮጵያ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው የከተማ አስተዳደሩ አዲስ ባወጣው አዋጅ መሠረት አምራች ኢንዱስትሪዎቹ እንዲከፍሉ የተጠየቁትን የቦታና የቤት ግብር በሦስት ቀናት ውስጥ ካልከፈሉ እንደሚታሸጉ የሚገልጸው ደብዳቤ ካለፉት ሁለት ሳምንታት ጀምሮ እንዲደርሳቸው እየተደረገ ነው፡፡

***https://www.ethiopianreporter.com/130953/***

### 3. ኤምባሲው በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉ የጃፓን ባለሀብቶችን ቁጥር ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ

ተጨማሪ የጃፓን ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በኢንዱስትሪ ፓርኮችና በድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና ኢንቨስት እንዲያደርጉ በትኩረት እየሠራ መሆኑን በኢትዮጵያ የጃፓን ኤምባሲ አስታወቀ፡፡

**ፋና ፣ ሰኔ 5፣ 2016**

በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ ጋር የተወያዩት የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አክሊሉ ታደሰ፤ የጃፓን ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮችና በድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና ኢንቨስት እንዲያደርጉ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

https://www.fanabc.com/archives/249413

### 5. ወደ አውሮፓ ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ ጠንከር ያለ ቁጥጥር መጀመሩን ባለሥልጣኑ አሰታወቀ

ከኢትዮጵያ ወደ አውሮፓ ኅብረት የሚላኩ ምርቶችን የአውሮፓ ኅብረት ባወጣቸው ጥብቅ መሥፈርቶች መሠረት ፈትሾ ለመላክ የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ጠንከር ያለ ቁጥጥር መጀመሩን አሰታወቀ። ባለሥልጣኑ እየጠበቁ ያሉ ዓለም የንግድ ሕጎችንና መሥፈርቶችን አሟልቶ መላክ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት የግብርና ምርቶችን ከእርሻ ጀምሮ ከአገር እስኪወጣ ደረስ የቁጥጥርና የምርመራ ሥራ መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**Reporter** ***June 30, 2024***

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወንድአለ ሀብታሙ እንዳመለከቱት የአውሮፓ ኅብረት ያወጣው ጠንካራ ሕግ በመሆኑ የኢትዮጵያ ምርቶች ወደ ውጭ ከመላካቸው በፊት እዚሁ በመመርመርና መሥፈርቱን ማሟላት አለማሟላታቸውን በመለየት ግድ ሆኗል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/130958/

### 6. የኮርፖሬሽኑና የኩባንያው ስምምነት – የሴራሚክ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አንዱ ተግዳሮት ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን በሚፈለገው ልክና ወቅት ማግኘት አለመቻል መሆኑ ይገለጻል:: እነዚህን ግብዓቶች ለማስገባት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ማግኘት አለመቻልም ሌላው ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል:: በተለይ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ማጠናቀቂያ ግብዓቶች በአብዛኛው ከውጭ የሚመጡ መሆናቸው ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዳይበቁ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ::

**Addise zemen : June 22, 2024**

የሴራሚክ ምርቶች በሀገር ውስጥ እየተመረተ ያለው በጣም ጥቂት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ/ እሱም በቅርቡ ነው መመረት የጀመረው /አብዛኛው የሴራሚክ ምርት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ እየተደረገ ነው ከውጭ የሚገባው::

**https://press.et/?p=130511**

### 7. በአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰቱ ተባዮች በሆርቲካልቸር ምርቶች ላይ ችግር እየተፈጠሩ መሆኑ ተገለጸ

የሆርቲካልቸር ምርቶችን የሚገዙ የአውሮፓ ኅብረት አገሮች የቁጥጥር ሥርዓታቸውን በማጠናከራቸው በላኪዎች ላይ ችግር እየተፈጠረ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

**Reporter** ***June 23, 2024***

በሆርቲካልቸር ምርት ጥራትና ደኅንነት ላይ ያተኮረ ብሔራዊ የምርት ጥራት ምዘና ጉባዔ ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ሲካሄድ የተገኙት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ድሪባ ኩማ (አምባሳደር) ገልጸዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/130694/

**8. የመጨረሻ የተባለው የንግድ ምክር ቤቱ ምርጫና የሚኒስቴሩ ውሳኔ**

የተለያየ ስያሜዎችን በመያዝ ወደ 80 ዓመታት የተጠጋ ዕድሜ ያለው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ባለፉት ሃያ ዓመታት ብዙ ውጣ ውረዶችን ያሳለፈ መሆኑ ይነገራል፡፡ በተለይ ንግድ ምክር ቤቶችን እንደገና ለማቋቋም ከሃያ ዓመታት በፊት የወጣው አዋጅ አጠቃላይ የንግድ ምክር ቤቱን የቀደመ የአሠራር ሥርዓት የለወጠ መሆኑ በሥራው ላይ ጫና እንዳሳደረ ሲገለጽ ቆይቷል፡፡

**Reporter *June 19, 2024***

አዋጁ ከረቂቅ ዝግጅቱ ጀምሮ ሲያጨቃጭቅ እንደነበር የሚታወስም ነው፡፡ አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላም ፈጠራቸው የተባሉ ችግሮች በአደባባይ ቢገለጽም አዋጁ ሳይሻሻል አሁን ድረስ ቆይቷል፡፡ አዋጁ መሻሻል እንዳለበት ታምኖ የማሻሻያ ሥራው ከተጀመረ ከአሥር ዓመታት በላይ የወሰደ ቢሆንም እስካሁን መቋጫ አላገኘም፡፡ በቅርቡ ግን ንግዱንና ኢንዱስትሪውን በመለያየት የየራሳቸው አደረጃጀት እንዲኖራቸው ተወስኖ ረቂቅ አዋጀቹ ለማፅደቅ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ተደርሷል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/130628/**

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

**9. FM Taye confers with Italian parliamentary delegation**

Ethiopia's Foreign Affairs Minister Ambassador Taye Atske Selassie, welcomed an Italian parliamentary delegation led by Senator Stefania Craxi, President of the Senate Foreign Affairs and Defense Commission.

**Ethiopian Herald: June 30, 2024**

During the discussion at the Foreign Minister's office, the two sides brought up bilateral, regional, and multilateral issues of mutual concern. While discussing bilateral issues, Ambassador Taye appreciated the Italian Government's realistic approach to supporting Ethiopia in a variety of sectors.
The two sides also noted Ethiopia and Italy's ever-growing relationship, according to Foreign Affairs Ministry.

**https://press.et/herald/?p=98086**

**10. Ethiopia to establish nuclear science and technology center**

Ethiopia has initiated a nuclear science and technology center aimed at leveraging the sector for peaceful purposes, including electricity generation. This new center will be sustainably managed to ensure long-term benefits.

**Capital Ethiopia: July 1, 2024**

As a member of the African Regional Cooperation Agreement for the Development of Nuclear Science and Technology Research (AFRA), Ethiopia is set to enhance its utilization of nuclear technology. This announcement was made by the Minister of Innovation and Technology at the 35th meeting of the AFRA Technical Working Group, which has been taking place in Addis Ababa over the past four days.
https://www.capitalethiopia.com/2024/07/01/ethiopia-to-establish-nuclear-science-and-technology-center/

**11. France reaffirms solidarity with Ethiopia on upcoming IMF agreement**

The French government has expressed its intention to continue supporting Ethiopia's economic reforms and the upcoming International Monetary Fund (IMF) agreement, reaffirming its solidarity with the East African nation.

**Capital Ethiopia: July 1, 2024**

During an event organized by the French Embassy in Ethiopia, French Ambassador to Ethiopia Remi Marechaux stated that the French government has backed the previous IMF agreement and the economic reforms launched in 2019. "We intend to do so in the soon-to-be-agreed, soon-to-be signed IMF agreement. So we intend to continue supporting this economic reform through the engagement of the French government agency," Marechaux said.
https://www.capitalethiopia.com/2024/07/01/france-reaffirms-solidarity-with-ethiopia-on-upcoming-imf-agreement/

**12. Ethiopia, South Sudan to build 220km cross-border road**

Ethiopia and South Sudan are set to build a 220-km cross-border road, following a $738-million financial agreement signed in May 2023.

**THE EAST AFRICAN JUNE 29 2024**

South Sudan's Transitional National Legislative Assembly on Tuesday ratified the Ethiopia-South Sudan financial agreement to build a cross-border highway, the Ethiopian Ministry of Foreign Affairs said in a statement Thursday.
The ministry said the project aims to enhance connectivity and bolster economic ties between the two neighboring countries, underscoring the growing cooperation and mutually beneficial relationship between Ethiopia and South Sudan.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/ethiopia-south-sudan-to-build-220-km-cross-border-road-4673872

13. **Cairo hosts Egypt-EU investment conference**

The Cairo meeting attended by President Abdel Fattah el-Sissi and EU commission Chief Ursula von der Leyen culminated in the signing of deals worth billions of dollars.

**African news: July 1, 2024**

The conference comes on the back of a $7.9 billion funding package agreed in March to support the North African country battle an economic crisis made worse by rising debt, inflation and currency shortages.
A series of small and medium term loans constitute the large majority of the package.
In exchange, Cairo must step up energy exports to Europe and action on irregular migrants. The EU has agreed similar deals with Tunisia, Mauritania and Libya, angering rights groups.

**https://www.africanews.com/2024/07/01/cairo-hosts-egypt-eu-investment-conference/**